# የወላጆች መመሪያ ለቀስ በቀስ መለያየቶች



## እንኳን ወደ አዲስ ለመጡት ልጆች እንክብካቤ (Care for Newcomer Children – CNC) በደህና መጡ

*እንኳን ወደ CNC መርሃ ግብራችን በደህና መጡ!*
*ልጅዎ ደህንነት እንዲሰማው/ት እና እርስዎ ያለምንም ጭንቀት ማጥናት እንዲችሉ፣ ከመርሃ ግብራችን እና ከሰራተኞች ጋር ለመለማመድ የተወሰነ ጊዜ መውሰድ አስፈላጊ ነው።*

*አንዳንድ ጊዜ ወላጆቻቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ጥለዋቸው ሲሄዱ ልጆች ይጮኻሉ፣ እራሳቸውን መሆን ያቅታቸዋል ወይም በጣም ስሜታዊ ይሆናሉ። ይህ የመለየት ጭንቀት የተለመደ ነው— በተለይ ልጅዎ በቡድን እንክብካቤ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ/ች። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁለታችሁንም ለማገዝ የመጀመሪያ ቀስ በቀስ መለየትን gradual separation በመጠቀም በጥንቃቄ እንከታተላለን።*

## ቀስ በቀስ መለየት ምንድን ነው?

ቀስ በቀስ መለየትን ማለት ልጅዎ በመርሃ ግብሩ ውስጥ የበለጠ እየተመ(ቸው/ቻት) ሲሄድ/ስትሄድ በወላጅ እና በልጅ መካከል ያለውን ተለይተው የሚቆዩበት ጊዜ መጨመር ነው። ከመርሃ ግብሩ ሠራተኞች ጋር መሥራት እና ልጅዎን ከጊዜው ቀደም ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመለያየት ማዘጋጀትን ያጠቃልላል።

**ቀስ በቀስ መለየት**፡

- የልጆችን ፍላጎቶች ያከብራል፣
- ልጅዎ ሰላም እና ደህንነት እንዲሰማው/ት ያግዛል፣
- ወደ እኛ መርሃ ግብር ቀላል ሽግግር እንዲኖር ያግዛል፣ እና
- ልጁ/ልጅቷ እያደገ/ች ሲሄድ/ሲትሄድ ለስኬታማ መለያየቶች እና ጤናማ የስሜት ግንኙነት መድረክ ይፈጥራል።

በመጀመሪያ መለያየቶች ከባድ የስሜት ቀውስ ያለባቸው ልጆች በመርሃ ግብሩ ውስጥ ለመረጋጋት ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳሉ፣ ስለሆነም እንደአስፈላጊነቱ ከልጅዎ ጋር ለመቆየት ዝግጁ ይሁኑ። እያንዳንዱ ልጅ የተለየ ነው፣ ግን ሂደቱን አለማጣደፍ በጣም አስፈላጊ ነው።

## እንዴት ነው የሚሠራው?

**ክፍል ከመጀመርዎ በፊት፡-**

- ከተቻለ የእኛን መርሃ ግብር ከልጅዎ ጋር ሆነው ይጎብኙ።
- ስለ ልጅዎ፣ ስለ መርሃ ግብሩ እና እንዴት አብዛኛውን ጊዜ ለመለያየት እንደሚያቅዱ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በአመችዎ ጊዜ ይወያዩ። ይህም ልጅዎ ሰራተኞችን ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስተማማኝ መሆኑን እንዲመለከት/እንድትመለከት ያግዛል።
- ከተቻለ ለልጅዎ የእርስዎ መማሪያ ክፍል የት እንደሆነ ያሳዩ።

**የልጅዎ የመጀመሪያ ጥቂት ቀናት**

- ዘና ለማለትና ፍላጎት ለማሳየት ይሞክሩ።
- ልጅዎ የበለጠ ሊያዝናናው/ት ይችላል ብለው የሚያስቡት ቦታ ይሂዱ እና ልጅዎ መጫዎት የሚወደው/የምትወድው ነገር ለሰራተኞች ይንገሩ።
- ልጅዎ ላይ ትኩረት ያድርጉ። ያነጋግሯቸው፣ የህጻናት መጫወቻዎችን ያሳዩዋቸው እና ከእነርሱ ጋር ይጫወቱ።
- ሊሳቡበት የሚችሉትን ሌሎች ቦታዎችን በንቃት ይከታተሉ እና የእነሱን መሪነት ይከተሉ።
- ከሠራተኞቹ ድርጊት ወይም የንግግር ምልክቶችን ይመልከቱ።
- ልጅዎ ዝግጁ በሚሆነበት/በምትሆንበት ጊዜ ከሌሎች ልጆች ወይም ከሠራተኛ ጋር እንዲጫወቱ ያበረታቱ። ልጅዎ ዝግጁ ካልሆነ/ች ትንሽ ጊዜ መጠበቁ ተገቢ ነው።
- ልጅዎ በራሳቸው ወይም ከሌሎች ጋር መጫወት በሚችልበት ጊዜ፣ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ተለያይተው ለመሞከር ዝግጁ ለመሆናቸው ጥሩ ምልክት ነው! ለመመልከት አንድ እርምጃ ወደ ኋላ ለመውሰድ ይሞክሩ።


*Funded by: Immigration, Refugees and Citizenship Canada / Financé par : Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada*

# የወላጆች መመሪያ ለቀስ በቀስ መለያየቶች

- ልጅዎ ወዲያውኑ ከተከተለዎት/ችዎት እና በአቅራቢያ እንዲቆዩ የሚፈልገው/የምትፈልገው ከመሰለዎት፣ እነርሱ ዝግጁ ላይሆኑ ይችላሉ።
- ጥቃት እና የስሜት መቃወስ ላጋጠማቸው ልጆች ሙሉ ለሙሉ መለያየት ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

**የመጀመሪያ መለያየቶች**

እርስዎ እና ሰራተኞች ልጅዎ በደንብ እየተጫወተ እና ምቾት የሚሰማው እንደሆነ ከተመለከታችሁ፣ መርሃ ግብሩን ለአጭር ጊዜ ትተው ለመሄድ መጀመር ይችላሉ።

- ወደ መጸዳጃ ቤት እንደሚሄዱ እና በሁለት ደቂቃዎች ውስጥ ተመልሰው እንደሚመጡ ለልጅዎ ይንገሩ።
- ፈጽሞ የሚሄዱበትን ለሰራተኞች ሳይነግሩ ክፍሉን ለቀቀው አይወጡ
- ወደ መጸዳጃ ቤት ይሂዱ እና ባሉት ጊዜ ተመልሰው መምጣትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
- ይህ የመጀመሪያ መለያዎት ለልጅዎ አስጨናቂ ከሆነ እነርሱ ዝግጁ ላይሆኑ ይችላሉ።

የመጀመሪያው የመለያያ ሁኔታ በጥሩ ከተከናወነ በኋላ፣ ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ (5-15 ደቂቃዎች) ለሁለተኛ ጊዜ ለመሞከር ዝግጁ ነዎት። እና ከዚያ ሶስተኛ ረዘም ያለ መለያያ (10-20 ደቂቃዎች)።

እነዚህ አጭር መለያያቶች የልጅዎን እምነት የሚገነቡ ከመሆኑም ሌላ ሁልጊዜ ተመልሰው እንደሚመጡ እንዲገነዘቡ ያግዟቸዋል። ለእያንዳንዱ መለያየት የሚከተሉትን ያረጋግጡ፡-

- ወጥነት ይኑርዎት።
- እየሄዱ እንደሆን ለልጅዎ ይንገሩ። ተደብቆ መውጣት መተማመንን የሚያፈርስ እና የወደፊት መለያየቶችን የበለጠ አስቸጋሪ ያደርጋል።
- ስንብትዎን በተቻለ መጠን አጭር ያድርጉ እና ሲሄዱ ልጅዎን የሚደግፍ ወጥ/የተለመደ የሰራተኞች አባል ይኑርዎት።
- ተመልሰው በሚመጡበት ጊዜ አዎንታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ትኩረት ያድርጉ። ልጅዎ የትኞቹ መጫወቻዎች እንደሚወዷቸው ወይም ምን የበለጠ እንደወደዱ ለመጠየቅ ይሞክሩ።

ልጅዎ እነዚህን አጭር መለያየቶች ያለ ብዙ መረበሽ ከፈጸመ/ከፈፀመች፣ እርስዎ እንዲሄዱ ዝግጁ ናቸው! ለመጀመሪያው መርሃ ግብር ሙሉ የጊዜ ርዝመት ልጅዎን ትተው መሄድ ሲጀምሩ፣ ሁሌም ተመልሰው የመምጣትዎን ሃሳብ ለማጠናከር መጥተው ከሚወስዱት ውስጥ ከመጀመሪያዎቹ መካከል አንዱ ለመሆን ይጣሩ።

**ልጄ የሚበሳጭ/የምትበሳጭ ከሆነስ?**

ልጅዎ አሁንም ችግር እያጋጠመው ከሆነ ላለመጨነቅ ይሞክሩ። ከልጅዎ ጋር በመርሃ ግብሩ ውስጥ ተጨማሪ ደህንነት እና ምቾት እንዲሰማቸው ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ ማሳለፍ ይኖርብዎታል። መጫወቻ ወይም ብርድ ልብስ ማምጣት፣ ወይም የአንገት ጥምጥም/ሻሽ/ሻርፕ ወይም ሹራብ መተው ልጅዎ የበለጠ ምቾት እንዲሰማው ሊያደርግ ይችላል።

የመርሃ ግብሩ ባለሙያዎች በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ቤተሰቦችን ረድተዋል እና እነርሱ እርስዎን ለመምራት እና ለመደገፍ እዚያ ይገኛሉ።

CMAS
ወጣት ፍልሰተኛ ህጻናት እንክብካቤ እና ስፈራ መደገፍ

ለበለጠ ወላጅ መርጃዎች ይጎብኙ፡-
www.cmascanada.ca

Care for Newcomer Children


*Funded by: Immigration, Refugees and Citizenship Canada / Financé par : Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada*